# ማዶልዶምን እንደ የትግል ስልት የቆጠሩት ጽንፈኞች

**ኢዛና ዘ መንፈስ 09-22-17**

ኢህአዴግ መራሹ የኢትዮጵያ መንግስት ወደ ስልጣን ከመጣ ጀምሮ የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በሀገራችን ህብረተሰብ ዘንድ ስር የሰደደ ችግር ስለመሆኑ ሲናገር ያልተደመጠበት አጋጣሚ የለም ማለት ይቻላል፡፡ ችግሩ በልማታዊ አስተሳሰብ እየተደፈቀ ካልሄደ በስተቀር የማህበራዊ ዕድገትና ብልጽግና ፀርነቱ ይበልጥ ተባብሶ ሊቀጥል የማይችልበት ምክንያት እንደማይኖርም ጭምር ከማስገንዘብ ቦዝነው የማያውቁ የኢፌድሪ መንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት ጥቂት አይደሉም፡፡

ይህ የገዢው ፓርቲ ዓመታትን ያስቆጠረ የፀረ ኪራይ ሰብሳቢነት አቋም እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ችግሩን በተግባር ከመታገል አኳያ እንብዛም ትርጉም ያለው ጥረት ሲደረግ የተስተዋለበት አጋጣሚ አለመኖሩ ግን በርካታ ዜጎችን ሲያነጋግርና ሲያከራክር መቆየቱ ይታወቃል፡፡ እናም የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የሚገለጽባቸው ፈርጀ ብዙ ችግሮች ከጊዜ ወደጊዜ ይበልጥ እየተበራከቱ በመምጣታቸው ምክንያት ጉዳዩ የፌደራል ስርዓቱን ለአሳሳቢ ቅልበሳ አደጋ ሊያጋልጥ ወደሚችል ደረጃ ሳይደርስ እንዳልቀረ ይታመናል፡፡ ይህ አስተያየት የተጋነነ መስሎ የሚሰማው አንባቢ ካለም ደግሞ፤ ሌላ ሌላውን ትተን ስልጣን ላይ ያለው ገዥ ፓርቲና እርሱ የሚመራው የኢፌድሪ መንግስት ባከሄዱት የትልቅ ተሃድሶ መድረክ ሲገለጽ የሰነበተውን እውነት ማስታወስ ብቻ በቂ ሆኖ ይሰማኛል፡፡

ምክንያቱም፤ የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በነሐሴ 2008 ዓ.ም ያካሄደውንና የግንባሩን የአስራ አምስት ዓመታት ጉዞ የገመገበትን አስቸኳይ ስብሰባ ሲያጠቃልል ባወጣው ድርጅታዊ መግለጫ ላይ ይፋ የሆነውን አቋም ማስታወስ እንደሚቻለው፤ በተለይም የመንግስት ስልጣንን ለግልና ለቡድን ጠባብ ፍላጎት ማሟያ ብቻ አድርጎ ለመጠቀም የመሻት አዝማሚያ በስርዓቱ መዋቅር ውስጥ እየተባባሰ ስለመምጣቱ የጋራ ግንዛቤ ተወስዶበታልና ነው፡፡ ይህ ማለትም ደግሞ "ኢህአዴግ መራሹ መንግስት የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ችግር አሳሳቢ የስርዓቱ አደጋ ሰለመሆኑ ከመናገር ቦዝኖ የማያውቀውን ያህል ለምን ችግሩን አምርሮ በመታገል ረገድ ቁርጠኛ አቋም አያሳይም?" ለሚለው የህዝብ ጣያቄ ከእስከ ዛሬው የተሻለ ምላሽ የሚሰጥ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል የግምገማ ውጤት ነው ብለን እንድናምን የሚጋብዝ ይመስለኛል፡፡

በሌላ አነጋገር፤ ይሄ መንግስት የሥነ ምግባራዊ ዝቅጠት መገለጫ ተደርጎ ስለሚወሰደው የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ተግባርና አስተሳሰብ አደገኛ ገጽታዎች አበክሮ ከማስገንዘብ ያለመቦዘኑን ያህል፤ ሙስናን በመታገል ረገድ የፖለቲካ ቁርጠኝነት አይስተዋልበትም የሚል ቅሬታ አዘል አስተያየት ለሚሰነዝሩ ወገኖች ጥሩ ምላሽ የሚሰጥም ጭምር ነው ማለት ይቻላል አሁን አሁን ገሃድ መውጣት የጀመረው እውነታ፡፡ እንዴት? ቢባልም ደግሞ፤ የኢፌድሪ መንግስት ሙስናን ከመታገል አኳያ ከእስከ ዛሬው ጥረቱ በተሻለ ስፋትና ጥልቀት ተንቀሳቅሶ አደጋውን ትርጉም ባለው መልኩ ለመቀልበስ የሚያስችል ተጨባጭ ውጤት ሳያስመዘግብ የቆየበት ዋነኛ ምክንያት፤ እዚሁ የፌደራል ስርዓቱ መዋቅር ውስጥ ተሰግስገው ፀረ ኪራይ ሰብሳቢነት ትግሉን የማዶልዶም አሉታዊ ሚና የሚጫወቱ

ጥገኛ ኃይሎች የሚፈጽሙት ደባ አላላውስ እያለው ነው ብለን እናጠቃልል ዘንድ የሚያስገድድ ጥሬ ሀቅ ላይ ደርሰናል ነው፡፡

ለዚህ አስተያየቴ የተሻለ ማሳያ ሊሆን ይችላል የምለውም የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ነሀሴ 15 ቀን 2008 ዓ.ም ባወጣው መግለጫ ላይ "ለመንግስት ስልጣን ያለን አረዳድ (አተያይ) እጅግ የተዛባ ከመሆኑ የተነሳ የተሰጠውን የስራ ኃላፊነት ለየራሱ የግል ጥቅም መሟላት በሚያመች መልኩ ብቻ ሲጠቀምበት የሚስተዋል የአመራር አካል ተበራክቷል፡፡ ይህ መሆኑም ደግሞ ህዝቡ ከመረጠው መንግስት የሚጠብቀውን መልካም አስተዳደርና ሌላም የሚያረካ የአገልግሎት አሰጣጥ በተግባር እንዳያገኝ እያደረገ ነው፡፡ ስለዚህም ከመቸውም ጊዜ ይልቅ ችግሮቻችንን ትርጉም ባለው መልኩ መርምረን ለመፍታት እንችል ዘንድ ጥልቅ ተሃድሶ ማካሄድ ያስፈልገናል" ሲል ማሳወቁን ተከትሎ በጽንፈኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች ጎራ የተፈጠረውን ብርቱ መደናገጥ ነው፡፡

ለአብነት ያህልም የጥልቅ ተሃድሰው ዜና ከተደመጠበት ቀን ጀምሮ፤ የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን የህልውናቸው መሰረት አድርገው የሚወስዱት የትምክህትና የጠባብ ብሔርተኝነት ቡድኖች፤ ትግሉን ለማዶልዶም ያለመ ዕከል የመፍጠር እንቅስቃሴያቸውን ከአገር ቤት እስከ ባህር ማዶ በተዘረጋ ግልጽና ስውር የጥፋት ተግባር መረባቸው አማካኝነት ሲያጧጥፉት የተስተዋሉበት እውነታ እንደነበር አይዘነጋም፡፡ በተለይም ደግሞ የአማራና የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልሎችን ግንባር ቀደም የኪራይ ሰብሳቢዎቹ ኃይሎች መፈንጫ ለማድረግ ከመፈለግ የመነጨ የሁከትና ብጥብጥ ተግባር በተስተዋለባቸው አንዳንድ አካባቢዎች፤ ነውጠኞቹ ቡድኖች በሰላማዊው ህዝብ ላይ ስላደረሱት የህይወትና የንብረት ኪሳራ ብዙ ተብሏል፡፡

እነርሱ የህልውናቸው መሰረት አድርገው የሚቆጠሩትን የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን አምርረን እንዳንታገል ለማድረግ ሲሉ ከአገር ቤት እስከ ባህር ማዶ ድረስ በዘረጉት የዕከል ፈጠራ መረባቸው አማካኝነት እየተመሳጠሩ የሚዶልቱት ፀረ ሕገ መንግስት ሴራ ሁሉ መክሸፉ ባይቀርም፤ ጽንፈኞቹ የተቃውሞው ጎራ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ መሪ ተዋናይ ኃይሎች ያንኑ ሀገር የማተራመስ ዕኩይ ተልዕኳቸውን "በአንድ ወይም ደግሞ በሌላ መንገድ" ለማሳካት ያለመ ደባ ከመፈፀም እንዳልታቀቡ ግን ሰሞኑን ከወደ ምስራቅ ኢትዮጵያ እየተደመጠ ያለው፤ ሁለት ወንድማማች ህዝቦችን በድንበር ይገባኛል ሰበብ ለማጋጨት ስለተሞከረበት ክስተት የሚያወሳ ዜና ጥሩ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ይመስለኛል፡፡

ምክንያቱም ደግሞ ይህቿን ሀገር የመምራት ታሪካዊ ኃላፊነት ተሸክሞ የተጀመረውን ፈርጀ ብዙ የህዳሴ ጉዞ ለማስቀጠል ያለመ ጥረት በማድረግ ላይ የሚገኘው የኢፌድሪ መንግስት ከፀረ ሙስና ትግሉ ጎን ለጎን "መጪው ዘመን የኢትዮጵያ ከፍታ ነው" የሚል መርሐ ግብር በመንደፍ ሀገር አቀፋዊ የልማት ንቅናቄውን ይበልጥ ለማጋጋልና አዲሱን የ2010 ዓ.ም በጀት ዓመት በተለየ የመነቃቃት መንፈስ ለመቀበል ሲንቀሳቀስ መስተዋሉ ያስደነገጣቸው ኪራይ ሰብሳቢዎቹ የተቃውሞው ጎራ ቡድኖችና እንዲሁም ለእነርሱ ሕጋዊ ሽፋን በመስጠት የሚታወቁት "የውስጥ አርበኞቻቸው" ይህን የብሩህ ተስፋ መንፈስ የሚያጨልም ዕኩይ ተግባር የመፈፀም ደባቸውን እንደተያያዙት

ይታመናልና ነው፡፡ በሌላ አነጋገር “መጪው ዘመንማ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት የከፍታ ሳይሆን ዕርስ በርስ የመተላለቅ ነው መሆን ያለበት” እንደማለት የሚቆጠር ሰማያዊ ቅናት ያደረባቸው ይመስላሉ በምስራቁ የሀገራችን ክፍል ከተከሰተው አሉታዊ ክስተት በስተጀርባ ያሉት ጽንፈኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች፡፡

ይህን ስንልም ደግሞ፤ የጽንፈኞቹ ተቃዋሚ ቡድኖች ህልውና፤ በኪራይ ሰብሳቢነት የፖለቲካ ኢኮኖሚ ላይ ብቻ የተመሰረተ እንደመሆኑ መጠን፤ በተለይም የመንግስት መዋቅር ውስጥ ተሰግስገው ለነእርሱ ድብቅ አጀንዳ መሳካት ድጋፍ የሚሰጡበትን ኢ-ፍትሐዊና ኢ-ስነምግባራዊ ድርጊት በመፈፀም የተጠመዱ ጉዳይ አስፈፃሚዎቻቸው እንዳይጋለጡና ሕግ ፊት እየቀረቡ እንደየጥፋታቸው ተጠያቂ የሚሆኑበት ግልጽ አሰራር በዚች አገር እንዳይሰፍን ለማድረግ ሲሉ የማይፈነቅሉት የከፋት ድንጋይ ሊኖር አይችልም ማለታችን ነው፡፡ እናም እነርሱ የሚናፍቁትን መንበረ ስልጣን በአቋራጭ መንገድ እንዲቆናጠጡ ካልተፈቀደላቸው በስተቀር፤ ለኢትዮጵያውያን ህዝቦች ዘለቄታዊ የጋራ ዕጣ ፈንታ መቃናት ስለሚበጅ ብሩህ ተስፋ ማሰብ እንኳን ተራ ምኞት ከመሆን አያልፍም ብለን እንድናምን ለማድረግ ያለመ ፈርጀ ብዙ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሴራቸውን በማውጠንጠን ተግባር ላይ የተጠመዱት ጽንፈኞቹ የትምክህትና የጠባብ ብሄርተኝነት ቡድኖች፤ ይልቁንም የፀረ ሙስና ትግሉን ሒደት በሚያዶለዱም ደባ መጠመድን እንደ “አዋጪ” የተቃውሞ ስትራቴጂ ከቆጠሩት ሰነባብተዋል፡፡

ከዚህ የተነሳም፤ የዛሬዋ ኢትዮጵያ ህዝቦች ድህነትና ኋላ ቀርነት የተሰኘ የጋራ ጠላታችንን ታግለን ለማሸነፍና በዚያው ልክም የህልውናችን ጽኑ መሰረት የተጣለባትን እናት ሀገራችንን ከአሳፋሪው የጨለማ ዘመን ታሪኳ አላቀን፤ ወደ ቀደመ ከፍታዋ ለመመለስ ስንል እጅ ለእጅ ተያይዘን የምናካሂደውን ዘርፈ ብዙ የፈጣን ልማት ግስጋሴ፤ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብም ጭምር ተገቢውን ዕውቅና እየቸረው የመምጣቱ ጉዳይ፤ ፅንፈኞቹ የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መሪ ተዋኒያን ቡድኖች ላይ ብርቱ ስጋት እንደፈጠረባቸው ይታመናል፡፡ ስለሆነም መላው የሀገራችን ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በሕገ መንግስታዊ የቃል ኪዳን ሰነዳቸው ላይ የተደነገገውን፤ ዕርስ በርስ ተፈቃቅዶ፤ ተከባብሮና ተፈቃቅሮ የመኖር ተጨባጭ ጠቀሜታ ይበልጥ እየተገነዘቡት ሔደው፤ አንድ ጠንካራ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ማህበረሰብን የመፍጠር ግባቸው መሳካቱ እንደማይቀር እርግጠኞች መሆን በጀመሩ ቁጥር ጽንፈኛ ተቃዋሚ ኃይሎች ወደ ለየለት የአጥፍቶ መጥፋት እርምጃ መግባታቸው የሚጠበቅ እንጂ አንብዛም የሚያስገርም ጉዳይ አይደለም፡፡

ይልቅስ እንደ እኔ እምነት ከሆነ፤ ከማስገረምም አልፎ ሊያስጨንቀን የሚገባው ቁልፍ ጥያቄ፤ መንግስታችን ጉዳዩን ከዚህ ስር ነቀል የሥርዓት ለውጥ ሂደቱን የማስቀጠልና ያለማስቀጠል መሰረተ ሃሳብ አኳያ ተረድቶ፤ ጽንፈኞቹ ተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች ሊፈጥሩብን ስለሚችሉት ዘርፈ ብዙ እንቅፋት አስቀድሞ ህዝቡን የማሳወቅና የጥፋት ተልዕኳቸው ቢሳካ ለየትኛውም ወገን የሚበጅ ድምር ውጤት ሊያመጣ እንደማይችልም ጭምር የማስገንዘብ ስራ መስራት አልነበረበትም ወይ? እውን አሁን አሁን ስር ነቀል የሥርዓት ለውጥ ሒደቱን ለመቀልበስ ያለመ ማንኛውንም የትግል መንፈስ የማጨለምና የማዶልዶም ስትራቴጂያቸውን ነድፈው ከባህር ማዶ እስከ አገር ቤት ድረስ በተዘረጋ የነውጠኝነት መረብ የተሳሰረ ዓለም አቀፋዊ የጥፋት ተግባር እንቅስቃሴያቸው አማካኝነት

የኢትዮጵያን የህዳሴ ጉዞ የሚፈታተን ዕክል ሲፈጥሩብን የሚስተዋሉትን፤ የትምክህትና የጠባብ ብሔርተኝነት ጽንፈኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች በማያሻማ መልኩ ከሕዝብ መነጠል አይቻልም ነበርን? የሚለው ነጥብ ይመስለኛል፡፡

በተለይም ደግሞ ሰሞኑን አንዳንድ የኦሮሚያ ክልል ምስራቃዊ ክፍል አካባቢዎችን ከኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ጋር በሚያዋስናቸው ስፍራዎች ላይ ተከሰተ የተባለውን ከወሰን ጋር የተያያዘ ግጭት፤ ከመቆስቆስ እስከ ማባባስ፤ የየክልላዊ መስተዳደሮቹ አንዳንድ አካላት አሉታዊ ሚና ነበረበት መባሉን ስንሰማ፤ የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን የህልውናቸው መሰረት አድርገው ከመውሰዳቸው የተነሳ የፀረ ሙስና ትግሉን ለማዶልዶም ያለመ ሴራ በማውጠንጠን ተግባር የተጠመዱ ጽንፈኞች እዚሁ በፌደራላዊ ስርዓቱ መዋቅር ውስጥ ተሰግስገው ከአትላንቲክ ውቅያኖስ ባሻገር ለሚገኙት የአስተሳሰብ አጋሮቻቸው በር የመክፈት ሙከራ የሚያደርጉበት ሁኔታ ስለመኖሩ ያመለክታል ባይ ነኝ እኔ በግሌ፡፡ ስለዚህ የወቅቱ እጅግ በጣም አንገብጋቢ ጥያቄ ተደርጎ መወሰድ ያለበትም፤ ለመሆኑ መጪው ዘመን የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ህዝቦች ከፍታ የሚረጋገጥበት ሀገራዊ ትንሳኤ ነው፤ የሚለውን የኢፌድሪ መንግስት መርሐ ግብር አንደጦር የሚፈሩት ጽንፈኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ልሂቃን፤ ከአትላንቲክ ውቅያኖስ ባሻገር ብቻ ነው ወይ ያሉት?

የኢትዮጵያ ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ማንኛውንም ዓይነት በመካከላቸው ሊነሳ የሚችል ጥያቄ ያለ ምንም ደም አፋሳሽ የዕርስ በርስ ግጭት ምላሽ እንዲያገኝ ማድረግ የሚችሉበት ሕገ መንግስታዊ ስርዓት ተዘርግቶ፤ ከቶውንም ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ ተግባራዊ እየሆነ በቆየባት ሀገር ውስጥ፤ ዛሬ ድንገት ብድግ ብሎ አንዱ ብሔር ከሌላኛው ወንድሙ ጋር እንዲቃቃርና በጠላትነት እንዲፈራረጅ የሚጋብዝ መርዘኛ ፕሮፖጋንዳውን ሲያዛምት የሚስተዋል የክልላዊ መስተዳደር ጋዜጠኛ፤ ወይም ደግሞ ሌላ ባለድርሻ አካል ካለ በእርግጥም እንደ ህብረተሰብ አብዝተን መስጋት ይጠበቅብናል፡፡ ለዚህ ለዚህማ የኦ.ኤም.ኤኑ ጃሐር መሐመድ፤ እንዲሁም ደግሞ የኢሳቶቹ እነ ኤርሚያስ ለገሰና የቪ.ኦ.ኤዎቹ እነትዝታ በላቸው ወዘተረፈ ምን ሰርተው ይብሉ ወገኖቼ? እንደኔ እንደኔ ግን የተጠቀሱት የጽንፈኞች ዲያስፖራ መገናኛ ብዙኃን በተጠና መልኩ እያቀነባበሩ የሚሰነዝሩብንን የሚዲያ ጦርነት መመከት ላይ ብንተባበር ነው የጋራ ህልውናችን በተመሰረተባት ሀገር ዘላቂ ዕጣ ፈንታ የሚበጅ ድምር ውጤት የሚኖረው የሚል ጽኑነት አለኝ፡፡ ስለሆነም ሁሉም ባለድርሻ አካላት ጉዳዩን ከዚህ መሰረተ ሃሳብ አኳያ ይገነዘቡልኝ ዘንድ አደራ እያልኩኝ ሀተታዬን አበቃሁ፡፡